## የሰሜን አፍሪካው ዐይነት መንግስታቱን ያናወጠና ፕሬዚደንቶች ከአገር እንዲባረሩ ያደረገ ህዛባዊ አመጽ በኢትዮጵያም ሊከሰት ይችላል ወይ?

ከሁለት ወር ተኩል በፊት አንድ ወጣት ቱኒዚያዊ የዩኒቨርሲቲ ትምህርቱን አጠናቆ የስራ ዕድል ለማግኘት ባለመቻሉና ፣ በፖሊሶችም የደረሰበት መንገላታት ስለበሳጨው ራሱን በማቃጠሉና ለሞት በመዳረጉ የተነሳ እንደምክንያት ሆኖ የተከሰተው ህዝባዊ እንቅስቃሴ ወደ ግብጽም እንደተዛመተና ፣ ፕሬዚደንት ሙባራክን ከስልጣናቸው እንዲባርሩ በማድረግ አካባቢውን አናግቶታል። ህዝባዊው እንቅስቃሴና ፕሬዚደንቶችን አባርሮ ስልጣን እንዲናጋ ማድረግ በሁለቱ አገሮች ብቻ ሳይወሰን ፣ ከሰላሳ ዐመት በላይ የመንን ይገዙ የነበሩትን ፕሬዚደንት ሳሌንን ፣ ቀጥሎም በሱኒት እስላም ሞናርኪ የምትዳደረውን ባህርይንና ወደ አልጄሪያ ፣ ሊቢያና ሌሎችም የአረብ አገሮች በመዛመት አካባቢውን እያመሰው ነው። እነዚህ የተለያየ ስም ይዘው አገሮቻቸውን ሲያስተዳድሩና እንዲያም ሲል የየአገሮቻቸውን ሀብት የውጭ አገር ባንኮች ውስጥ በማስቀመጥ የተንደላቀቀ ኑሮ ይኖሩ የነበሩት እንደዚህ ዐይነት በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደገፈ እንቅስቃሴ በመምጣቱና ስርዓቱን ማናጋቱ የእግዜአብሄር ወይም የአላህ ቁጣ ነው የመሰላቸው። ስልጣናቸውን ለልጅ ልጆቻቸው በማስተላለፍ ለዝንተ-ዓለም የሚገዙ መስሎአቸው ነበር።

የየፕሬዚደንቶችን በአጭር ጊዜ ውስጥ እንዲባረሩ ማድረግና ስርዓቱን ማናጋቱ በፖለቲካ ተንታኞች ዘንድ የተለያየ ትርጉም ተሰጥቶታል። በእኛ ኢትዮጵያውያን ምሁሮች ዘንድም እንደዚሁ እንደ አመለካከታችን የአገዛዞችን መገርሰስ በተለያየ መልክ እንድንተነትነው ተገደናል። የተወሰኑ የፖለቲካ ተንታኞች የተከሰተውን ሁኔታ ከንጹህ የኢኮኖሚ ጥያቄና ወጣቱም በስራ እጦት ምክንያት የደረሰበትን በደል ለመግለጽ በመፈለጉ ከየአገሩ መንግስታት ጋር የፈጠረው ግጭት ነው ሲሉ ፣ ሌሎች ተንታኞች ደግሞ እንደዚህ ዐይነት እንቅስቃሴ በነዚህ አገሮች ብቻ ቢከሰትም ፣ አጠቃላዩ የነዚህ አገሮች የአገዛዝና የኢኮኖሚ አወቃቀር ከዓለም አቀፋዊ የግሎባል ኢኮኖሚና የፖለቲካ አወቃቀርና በጥብቅ በመተሳሰሩ የተፈጠረ የተዛባ ሁኔታ ምክንያት ነው ይላሉ። በሌላ አነጋገር ፣ ከአለፉት ሰላሳ ዐመታት ጀምሮ በዓለም አቀፍ በከፍተኛ ደረጃ የሚካሄደው የግሎባል ኢኮኖሚ እንቅስቃሴ በተለይም በብዙ የሶስተኛው ዓለም አገሮች ውስጥ ኢኮኖሚያዊ መዛባትን ፣ የህብረተሰብና የባህል ውድቀትን ፣ በዚያውም መጠን የመንግስት አውታሮች መጠናከርና አገዛዞቹ የህዝብ አለኝታ ከመሆን ይልቅ ለራሳቸው ብቻና በራሳቸው ዓለም ውስጥ መኖር የግዴታ አገሮች ወደ መፋጠጫ መድረክ እንዲለወጡ እንዳደረጋቸው ያመለክታሉ። አብዛኛዎቹ ፣ እነዚህ ህዝባዊ እንቅስቃሴና አመጽ የተከሰተባቸው አገሮች ፣ በአሜሪካና በተቀረው የምዕራቡ ካፒታሊስት ዓለም የፀረ-ሽበርተኞች አጋዦችና የገበያ ኢኮኖሚ አራማጆች ተብለው ሲወደሱ ፣ በዚያው መጠንም ዕርዳታ በገፍ ይፈስላቸው እንደነበር በግልጽ ይታወቃል። የመጨቆኛ መሳሪያዎቻቸውን ፣ የስለላ ድርጅቶችንና ፖሊሱን እንዲሁም ወታደሮችም ሳይቀሩ ከአሜሪካን በሚመጣ ዕርዳታና ምክር የታጠቁና የሚደገፉ እንደነበር ራሳቸው „ርዳታውን“ የሚለግሱት የምዕራብ መንግስታት በግልጽ ይናገራሉ። ለምሳሌ የፕሬዚደንት ሙባራክ መንግስት ለወታደር ዕርዳታ ብቻ በዐመት ከአሜሪካ ከአንድ ቢሊዮን ተኩል ዶላር በላይ እንደሚያገኝና ፣ ሌሎችም ዕርዳታዎች እንደሚፈሱለት የታወቀ ጉዳይ ነው። ፕሬዚደንት ሙባራክ ሊወድቁ ወደ መጨረሻው ገደማ ሲደርሱ ፣ የምዕራቡ ማስ ሚዲያዎች ፕሬዚደንቱ በውጭ አገር ባንኮች ውስጥ ወደ ሰባ ቢሊዮን ዶላር የሚጠጋ ገንዘብ እንዳከማቹ ተናግረዋል። በዚህ ዐይነቱ ሀብትን ዘረፋና አገርን ማራቆት የየፕሬዚደንቶቹ ሚስቶችም የማይናቅ ሚና እንደተጫወቱና ፣ በተለይም የፕሬዚደንት ቤን ዓሊ ባለቤት ሊወጡ ሲሉ በቀጥታ ወደ ማዕከላዊ ባንኩ በማምራት እዚያ የተከማቸውን ወርቅ ዘርፈው እንደወጡ ተመዝግቧል።

ለየፕሬዚደንቶቹ እንደምሶሶ ሆኖ ደግፎ የያዛቸው በውጭ ድጎማ የሚረዳው ወታደርና የስለላ ድርጅት ሲሆን ፣ እነዚህ ሁለት መንግስታዊ አውታሮች የየፕሬዚደንቶች የአጥንት ጀርባ ከመሆን አልፈው ኢኮኖሚውን የሚቆጣጠሩና ከበርቴያዊ መደብ

እንዳይዳብር መንገዱን በመዝጋት ለኢኮኖሚና ህብረተሰብአዊ ቀውስ ዐይነተኛ ምክንያት እንደሆኑ በግልጽ ይታወቃል። በተለይም የወታደሩ ሚና በግብጽ የጎላ ሲሆን ፣ ካለሱ ፈቃድ የሚደርግ እንቅስቃሴ አልነበረም ማለት ይቻላል። በዚህ በታፈነ ሁኔታ የመንግስቱ አካል ኢኮኖሚውን በጥብቅ በሚቆጣጠርበት አገር ውስጥ በራስ አነሳሽነት ኢኮኖሚው ውስጥ በነጻ ተሳትፎ ለህብረተሰቡ የሚጥቅም የስራ መስክ መክፈትና ሀብት መፍጠር አይቻልም። የቱሪስት መስኩ ደግሞ ሙሉ በሙሉ በውጭ አገር ጎብኝዎች ላይ የተደገፈ በመሆኑ ገቢው እንደየሁኔታው ከፍና ዝቅ የሚል ሲሆን ፣ እንደዚህ ዐይነት የአገዛዝ ቀውስ ሲከሰት ገቢው በከፍተኛ ደረጃ እንደሚቀንስም መገንዘብ ይቻላል። ህዝባዊ እንቅስቃሴው ከተከሰተ ወዲህ በቱኒዚያም ሆነ በግብጽ ከቱሪስት የሚገኘው ገቢ ከሰባ በመቶ በላይ እንደቀነሰና አንዳንድ ሆቴል ቤቶች ደግሞ በመቶ ፐርሰንት ገቢያቸውን እንዳጡ ይነገራል።

በአንዳንድ ተንታኞች የሚነሳው ጥያቄ ፣ ሁኔታው እንደዚህ በብርጭቆ ውስጥ እንደሚታይ የምንጭ ውሃ ግልጽ ከሆነ ሰለጠንኩ የሚለውና ዲሞክራሲን በዓለም አቀፍ ደረጃ እንዲስፋፋ ፣ እንዲያም ሲል የገበያ ኢኮኖሚ እንዲያብብ እታገላለሁም እደግፋለሁም የሚለው የምዕራቡ ዓለም በነዚህ አገሮች የሚታየው በስልጣን መባለግና በተወሰነ አካባቢ ብቻ ሀብት መከማችና ያልተስተካከለ ዕድገት ጉልህ ሆኖ እያለ ለምን ይህንን የተዛባ ሁኔታ ማየት ተሳነው? የሚል ነው። ብዙዎቹ ተንታኞችና አንዳንድ ቀና የፓርሊሜንታሪ ተጠሪዎች እንደሚሉት ሰለጠንኩ በሚለው የምዕራቡ ዲሞክራሲና እነዚህ አምባገነን ተብለው በሚጠሩት መንግስታት መሀከል ያለው ግኑኝነት የታወቀ ሲሆን ፣ በየአገሮች ውስጥም የሚካሄደው የሀብት ዘረፋና የጭቆና አገዛዝ ለምዕራቡ መንግስታት ድብቅ አይደለም የሚል ነው። ስለዚህም ይላሉ ፣ በመሀከላቸው ያለው ግኑኝነት የእከክልህ እከክለኝ ዐይነት ግኑኝነት ነው የሚሉት። ስለሆነም ፣ አንዳች ነገር እስካለተከሰተ ድረስ የምዕራብ መንግስታት እነዚህን ዐይነት የመሳሰሉ መንግስታት ስልጣን ላይ ለርዥም ጊዜ ቢቆዩ ደስታውን አይችሉትም የሚል ነው። ለውጥም ቢመጣም እንኳ ሁኔታው ከነሱ ቁጥጥር ስር እንዳይወጣ የማይገለብጡት ዲንጋይ የለም ብለው ነው በግልጽ የሚነግሩን።

ነገሩን ይበልጥ ለመረዳት ጠጋ ብሎ መመልከት ያስፈልጋል። ምክንያቱም በአንዳንድ የዋሆችና ስልጣን ላይ ቁጥጥ ብለው በዲሞክራሲ ስም ባለሰለሰ መልክ ፣ ይሁንና ደግሞ የድሮው ዐይነት አገዛዝና ፀረ-ዕድገት ፖሊሲ እንዲቀጥል ለሚፈልጉ የፕሬዚደንቶች በህዝባዊ አመጽ መወገድ ሰፊው ህዝብ የሚጠብቀውንና የሚፈልገውን ዐይነት ዕደገትና ዲሞክራሲ ተግባራዊ ሊያደርግ ይችላል ተብሎ ስለሚገመትና ስለሚታመን ነው። እንደዚህ ዐይነቱ ዕምነት በሰማኒያዎቹ ዐመታት በላቲን አሜሪካና በፊሊፒን የሚሊተሪና የሲቪል አምባገነን መሪዎች ስልጣናቸውን እንዲለቁ ከተገደዱ በኋላ በነዚህ አገሮች ብልፅግናና ዕውነተኛ ህዝባዊ ዲሞክራሲ ሊሰፍኑ አልቻሉም። ለምሳሌ አርጀንቲናን ብነወስድ ከሚሊታሪ አምባገነን አገዛዝ በኋላ የሶሻል ዲሞክራሲ ፓርቲ መሪ ስልጣኑን ቢይዙም ፣ የአርጀንቲና ህዝብ ቀደም ብሎ በሚሊታሪው አምባገነን አገዛዝና በዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት እንዲሁም በዓለም አቀፍ የፊናንስ ካፒታል ከተዋቀረው የኢኮኖሚ ፖሊሲና ዕዳ ትብትብ በፍጹም ልትላቀቅ አልቻለችም። ከዚያ በኋላ የወለድ ወለድ ከፋይ ብቻ ሳትሆን የዋጋ ግሽበትን እቋቋማለሁ በሚል የውጭ ገንዘቧን ከዶላር ጋር በማጣመርና ኢኮኖሚዋንም ዶላራይዝ በማድረግ ብሄራዊ-ነፃነቷን እንደተገፈፈች ይታወቃል። ሀብቷ ተዘርፏል ፤ ህዝቧም ወደ ድህነት ዓለም ተወርውሯል። ዕዳውንም ጨርሳ ብትከፍልም እንኳ በዓለም አቀፍ ድርጅት ስሌትና በፊናንስ ኦሊጋርኪ ስሌት የዘልዓለም ዕዳ ከፋይ በመሆን ከጦሱ እስካሁን ድረስ በፍጹም ልትላቀቅ አልቻለችም። የሀርባርድ ዩኒቨርስቲ የኢኮኖሚ ምርቶች የሆኑት የአርጀንቲና ተወላጆች የኢኮኖሚና የፊናንስ ሚኒስተሮች በመሆን የአርጀንቲናን ኢኮኖሚ በጠና መሰረት ላይ አዋቅሮ ኢኮኖሚውን ከመገንባትና ለህዝቡ ተስፋ ከመስጠት ይልቅ ፣ የዓለም አቀፍ ፊናንስ ካፒታል አቀንቃኝ በመሆን ኢንዱስትሪውን ለማፈራረስ በቅተዋል። ብራዚልም በሰማኒያዎቹና በዘጠናዎቹ ዐመታት የደረሰባት ስቃይ ተመሳሳይ ሲሆን ፣ በተመሳሳይ የኒዎ-ሊበራል ኢኮኖሚ ፖሊሲ አማካይነት የውስጥ ሀብቷን ወደ ውጭ ለማስተላለፍ በመገደዷና ኢኮኖሚዋም እንዲዘበራረቅ በመደረጉ ነው። በእንደዚህ ዐይነቱ የኢኮኖሚ ፖሊስ የኋላ ኋላ ባሸናፊነት ሊወጣ የቻለው የስኳር

ተከላንና ሶያ ቦንን የሚቆጣጠረውና በቤንዘን ምርት ላይ የተሰማራው የህብረተሰብ ክፍል ኃይል ብቻ ነው። የፕሬዚደንት ሉላ የስምንት ዐመት አገዛዝ ይህንን የህብረተሰብ ክፍል እንዲጠነክር በማድረግ በሶሻል ድጎማ አሳቦ ድህነቱ እዚያው በዚያው እንዲጠነክር አደረገው እንጂ የብራዚልን ኢኮኖሚ ስትራክቸራል ድክመትና የህብረተሰብ አወቃቀር በፍጹም አልቀየረውም። ምክንያቱም የፕሪዚደንት ሉላ የኢኮኖሚ ፖሊሲ አማካሪዎች በሙሉ የኒዎ-ሊበራል ርዕዮተ-ዓለም አመለካከት ያላቸውና በዚያው ፖሊሲ ብቻ በመመራት ሁኔታው ተድብስብሶ እንዲቀርና የህብረተስቡ አወቃቀርም በዚያው ረግጦ እንዲቆይ ስለሚፈልጉ ነው።

ይህ የሚያረጋግጠው ምንድነው? ከሃምሳዎቹ ዐመታት ጀምሮ በዓለም አቀፍ ደረጃ የተዘረጋው የአገዛዝ መዋቅርና ተግባራዊ የሆነው የኢኮኖሚ ፖሊሲ በሙሉ የሶስተኛውን ዓለም አገሮች በሁለት እግራቸው ቆመው እንዲሄዱና ሙሉ በሙሉ ነፃነትን እንዲቀዳጁ በሚያደርጋቸው መልክ ባለመዘጋጀቱና ባለመደራጀቱ ነው። በሶስተኛው ዓለም አገሮች የተዘረጉት የአገዛዝ መዋቅሮች በሙሉ ከየአገሮች ሁኔታ በመነሳት ከታች ወደላይ ቀስ በቀስ ብለው ያደጉ ፣ ሳይሆን በካፒታሊስት አገሮች ምክር የነሱን ጥቅም በሚያስጠብቁ መልክ የተደራጁ ናቸው። በብዙ የሶስተኛው ዓለም አገሮችም በልዩ ልዩ መልክ የሚገለጽ ምሁራዊ እንቅስቃሴ ባለመኖሩ ካለምንም ትችት ለካፒታሊስት አገሮች የሚያመቹ የአገዛዝ ሰንሰለት መዘርጋትና በቀላሉ ማኒፑሌት ማድረግ ይቻላል። የሲቭልና የሚሊታሪ ቢሮክራቶችን ለተመለከተ ፣ አብዛኛዎቹ ከፍተኛ ትምህርት ቢማሩም ይህ ማለት ግን ጭንቅላትን በሚያጸዳ ዕውቀት የተካኑና ብሄራዊ ስሜትንና የአገርን ፍቅርን ያካባቱና እንዲሁም ህብረተሰብአዊ ኃላፊነት ተሰምቷቸው ወደ ውስጥ ያተኮረ ሁለገብ ፖሊሲ ይወስዳሉ ማለት አይደለም። ይህንን ሁኔታ በአናሎጊ መልክ ከምዕራብ አውሮፓ የባህልና የኢኮኖሚ ታሪክ ጋር እያወዳደሩ መመልከቱ ግንዛቤ እንዲኖረን ያስችለናል። ለምሳሌ የፕሮፌሰር ባሪንግተን ሙርን ዘ ሶሻል ኦሪጂን ኦፍ ዲክቴተርሺፕ(Barrinton Moor; The Social Origin of dictatorships) የሚለውን መጽሀፍና የማክስ ቬበርን ስራዎችና የሬናሳንስ ጽሁፎችን ላገላበጠ ትላንትም ሆነ ዛሬ በብዙ የሶስተኛው ዓለም ተብለው በሚጠሩት አገሮች ያሉትን የህብረተሰብ አወቃቀርን መረዳት ይቻላል። ይህን ዐይነቱን ኮምፓራቲቭ ስተዲይስ ሳያደርጉ ያለውን ችግር በሊበራሊ ዲሞክራሲ መነጽር ብቻ ለመመልከት መሞከር ልንወጣ ወደማንችለው ማጥ ውስጥ ይከተናል። ብዙ ጥናቶችና የህብረተሰብ ታሪክ ሂደት እንደሚያረጋግጠው ፣ በተቀነባበረ መልክና በተጠና ስልት እነዚህን በመሳሰሉ አገሮች የተዘረጋውን ፀረ-ዕድገት አገዛዝና አወቃቀሩን ሰባብሮ መሰረታዊ ለውጥ ማምጣት እስካልተቻለ ድረስ ፕሬዚደንትን በማውረድና በሌላ በመተካት ፣ እንዲሁም የኒዎ-ሊበራል አመለካከት ባላቸው ወይም ሊበራል ሳይሆኑ ሊበራል ነን በሚሉ ህዝባዊ እንቅስቃሴን ማስነጠቅ የድሮው ዐይነት አገዛዝ በሌላ መልክ እንዲቀጥል ማገዝ ይሆናል። ሌላው አማራጭና ቀናው መንገድ ደግሞ የግዴታ በሬናሳንስ ርዕይ የተመሰረተ ሰፊ የባህል ለውጥ ማካሄድ ነው። ሁለተኛው መንገድ ለጊዜው አድካሚ ቢመስልም ዘላቂና አጥጋቢ መፍትሄ ሰጥቶ የአንድን አገር ህዝብ አስተሳስሮ ወደ ተረጋጋ የስራ ዓለም የሚያመራ ነው። ሁለቱም መንገዶች የግዴታ የውጭ ኃይሎችንና የዓለም አቀፍ ኢንስቲቱሽኖችን ጣልቃ-ገብነት አጥብቀው ይቃወማሉ። ሁለቱም መንገዶች ፣ የአብዮታዊም ሆነ የሬናሳንስ የግዴታ የህዝብን በዲሞክራሲያዊ ውይይት መሳተፍንና የግዴታ በቀጥታ በአገር ግንባታ ውስጥ በንቁነት መካተትን ይጠይቃሉ። ይህም ማለት ሜዳውን አወቅን ለሚሉና ትግሉን ለሚያጨናግፉ ንዑስ ከበርቴዎች በፍጹም መለቀቅ የለበትም ማለት ነው።

ከእንደዚህ ዐይነቱ የአገዛዝና የህብረተስብ አወቃቀር ተነስቶና ፣ በተለይም ከ1950ዎቹ ዐመታት ጀምሮ እስካሁን ድረስ በዓለም አቀፍ ደረጃ የተስፋፋውን የካፒታሊስት ኢኮኖሚ ስንመለክት በቀላሉ የምንረዳው ፣ ስርዓቱ ስልጣኔን አምጭና ነፃነትን የሚያጎናጽፍ ሳይሆን በዓለም አቀፍ ደረጃ ድህነትን ፈልፋይ ነው። ይህንን ለመገንዘብ ደግሞ በተለይም ከሁለተኛው ዓለም ጦርነት በኋላ የተዋቀረውን ዓለም አቀፋዊ የስራ ክፍፍልና በየአስር ወይም በየሃያ ዐመታት ለሶስተኛው ዓለም አገሮች ተብሎ የሚዘጋጀውንና ፣ በእነ ዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅትና ዓለም ባንክ አማካይነት እየተገደዱ ተግባራዊ የሚያደርጉትን ወደ

ወጭ የሚያተኩር የኢኮኖሚ ፖሊሲ ጠጋ ብሎ መመልከት ያስፈልጋል። በተለይም ከ1980ዎቹ ዐመታት መጀምሪያ ጀምሮ ተግባራዊ እየሆነ የመጣው የኒዎ-ሊበራል የኢኮኖሚ አጀንዳና አዲሱ ግሎባላይዜሽን ይበልጥ የሶስተኛውን ዓለም አገሮች ኢኮኖሚዎች ጥገኛና ዝርክርክ ሆነው እንዲቀሩ አስገዳዳቸው። በዓለም አቀፍ ደረጃ የተዘረጋው የፋናንስ አወቃቀርና የሶስተኛው ዓለም አገሮችን ጥሬ-ሀብት መቆጣጠር በየአገሮቹ ውስጥ በሁሉም አቅጣጫ መዛባትን(Imbalances) ፈጠረ። የፊናንስ ካፒታል የበላይነትና የዓለም የገንዝብ ድርጅት(IMF) ተጠናክሮ መውጣትና የብዙ አገሮችን የኢኮኖሚ ፖሊሲ ደንጋጊ መሆን ከውስጥ ያለውን ህብረተሰብአዊ መዛባትና ድህነትን የበለጠ አሰፋው ፣ አጠናከረው። በማኑፋክቱር ላይ የተመሰረተ የኢኮኖሚ ዕድገት ማካሄድ አልተቻለም። ብዙ አገሮች ስነ-ስርዓት ያላቸው ከተማዎችን መገንባት አልቻሉም። ለስራ መከፈት የሚያመች የስራ-ክፍፍል ማዳበርና ማዋቀር አልተቻለም። ብዙ አገሮች ያላቸውን የእርሻ ሀብት ለመጠቀም ባለመቻላቸው ራሳቸውን በምግብ እንዳይችሉ ተገደዱ። በዚህ መልክ ደግሞ ወደ ውስጥ የገበያ ኢኮኖሚን ማዳበርና የገንዝብ በፍጥነት መሽከርከርን ማዳበር አይቻልም። የስራ ክፍፍል ካልዳበርና የንግድ መስኩ በገንዝብ አማካይነት ከሌሎች የኢኮኖሚ ዘርፎች ጋር ካልተያያዘና ፣ ገንዝብም በፍጥነት የማይሽከረከር ከሆነ ፣ ገንዝብ ህብረተሰብአዊ ኃይልን ሊያገኝ አይችልም ማለት ነው። ይህም ሁኔታ የገንዝብን ዋጋ መድከም ወይም የመግዛት ኃይልን መቀነስን ያስከትላል። ስለዚህም ነው በብዙ የሶስተኛው ዓለም አግሮች ያለውን ኢኮኖሚ ዐይነት በተራ የኒዎ-ሊበራል ኢኮኖሚ ቲዎሪ መግለጽ የማይቻለው። በሌላ አነጋገር ፣ በብዙ የሶስተኛው ዓለም አገሮች ሳይጠና የገባው ይበልጥ በገንዝብ ላይ የተደገፈ ፣ ግን ደግሞ የገንዘብን በፍጥነት መሽከርከር የሚያግድ የካፒታሊስት ኢኮኖሚ ፣ የየአገሮችን ኢኮኖሚ ውስጠ-ኃይል እንዲኖራቸው ከማድረግ ይልቅ ዘለዓለማዊ የተቀዋም ቀውስ(Structural Crisis) እንዲኖራቸው በማድረግ እዚያው በዚያው እንዲንደፋደፉ አደረጋቸው።

ከዚህ አጭር ትንተና ስንነሳ ከሁለት ወር ተኩል ጀምሮ በሰሜን አፍሪካና ወደፊትም ወደ ሌሎች የአፍሪካ አገሮችና ወደ ኢትዮጵያ ሊዛመት የሚችለውን ህዝባዊ እንቅስቃሴ ከላይ ውስጥ ለውስጥ ሲብላላና ህዝቦችን ሲያምስ ከከረመው ዓለም አቀፋዊ የኢኮኖሚና ፓለቲካዊ አወቃቀር ጋር ማያያዙ የአገራችንንም ሆነ የተቀሩትን የአፍሪካ አገሮች ችግር መረዳት እንችላለን። ይህንን ስንረዳ ብቻ በሰሜን አፍሪካ አገሮች የተነሳውንና በሌሎች የአፍሪካ አገሮችም ወደፊት ሊከሰት የሚችለውን ህዝባዊ እንቅሰቃሴ የቱን ያህል የተውሳሰበ ችግር ውስጥ እንደወደቀ መገንዘብና ትክክለኛ የትግል ስትራቴጂም መንደፍ እንችላለን። ይሁንና ደግሞ እንደዚህ ዐይነቱን የተወሳሰብ ችግር መገንዘብ የምንችለው ቀና አስተሳሰብ ሲኖረንና ቡድናዊ ስሜትን ከጭንቅላታችን በማስወገድ በንጹህ ምሁራዊ መነጽር መመልከት የቻልን እንደሆን ብቻ ነው። ይህ በራሱ ደግሞ ግለሰባዊ ነጻነትንና በራስ መተማመንን ይጠይቃል። ወደ አገራችን ሁኔታ ደግሞ እናምራ። አንዳንዶች የፖለቲካ ተንታኞች የሚሰጡትን አስተያየት ጠጋ ብለን እንመልከት።

እንደዚህ ዐይነቱ ህዝባዊ እንቅስቃሴና ፕሬዚደንቶችን አባሮ ስልጣንን ማናጋት በሰሜን አፍሪካና በአንዳንድ አረብ አገሮች ብቻ ሳይወሰን ወደ ሌሎች የምዕራቡ መንግስታት ተቀዋያ ወደሆኑ አፍሪካ መንግስታትም ዘንድ እንደሚደርስ አንዳንድ ተንታኞች ቁልጭ አድርገው ያስቀምጣሉ። ለምሳሌ አልበርት ሚቼል የሚባለው የፖለቲካ ተንታኝ ፣ የብዙ አፍሪካን መንግስታትን የተዛባ አገዛዝና በሙስና መተብተብ ከተነተነ በኋላ ፣ የዚህ ጽዋ ከሚደርሷት አገሮች አንዷ ኢትዮጵያ እንደሆነች ያመለክታል። በሱም አገላለጽ ፣ በስልጣን መባለግ ፣ ሆን ብሎ ብሄረሰቦችን አስታኮ የሚካሄድ የከፋፍለህ አገዛዝና የእርስ በርስ ግጭት ፣ በገዢው መደብና በካድሬዎች አማካይነት የማያስፈልግ የሃይማኖት ቅራኔ ፈጥሮ ወንድማማች ህዝብ እርስ በርሱ እንዲጨራረስ ማድረግ ፣ በኢኮኖሚው በስነ ስርዓት አለመደራጀትና ቀውስ መፈጠር የተነሳ የወጣቱ ተስፋ መቁረጥና ባልባሌ ቦታዎች መሰማራት ፣ እንዲሁም የተንዛዛ ሙስና የአገዛዙ ዐይነተኛ ባህርይ መሆን ፣ እነዚህ ሁሉ ለማይቀረው ህዝባዊ እንቅስቃሴዎች ዐይነተኛ ምክንያቶች ናቸው ይላል። ከሶስት ሳምንት በፊት አዲስ አበባ የሚገኙት የአሜሪካው አምባሳደር ለህዝባዊ አመጽ ሁኔታው

እንዲያውም ከቱኒዚያና ከግብጽ በተሻለ መልክ አመቺ እንደሆነና ፣ ይህም ስለስጋቸው እንደ ግብጽና ቱኒዚያ ህዝባዊ አመጽ እንዳይመጣ የተቃዋሚ ኃይሎችን አንድ ሆቴል ውስጥ ሰብስበው እንዳነጋገሯቸው ይታወቃል። ይህም ማለት አሜሪካንም ሆነ የተቀረው ምዕራብ አውሮፓ „ለአካባቢው መረጋጋት" ዐይነተኛ ሚና ይጫወታል የሚባልለት የአቶ መለስ መንግስት እንዳይወድቅ አስፈላጊውን ዕርዳታ ማግኘት እንዳለበት የውስጥ ለውስጥ ከፍተኛ ስራ ይሰራል ማለት ነው። ሰለጠንኩኝ የሚለው የምዕራቡ ካፒታሊስት ዲሞክራሲ የኢትዮጵያ ህዝብ በድህነትና በጭቆና አገዛዝ ዘለዓለሙን ፍዳውን ቢያይ ደንታው አይደለም ማለት ነው። በተጨማሪም ፣ በአሜሪካ የሚኖሩት የታወቁት የታሪክ ተመራማሪና ምሁር ፕሮፌሰር ገብሩ ታረቀ ከሶስት ሳምንት በፊት ከሪፖርተር ጋዜጣ ጋር ባደረጉት የጥያቄና መልስ ውይይት ለቀረበላቸው ጥያቄ ሲመልሱ ፣ የኢትዮጵያ ሁኔታ በብዙ እጥፍ ከግብጽና ከቱኒዚያ ጋር ሲወዳደር የባሰ እንደሆነ ይናገራሉ። በአገላለጻቸውም ፣ እንደ ኢትዮጵያ ያለ ህዝብ የተጨቆነና በድህነት የሚሰቃይ የለም ፤ እንዲያውም ይባስ ብሎ ሁኔታው ከሃይቲ እንደሚብስ አስመረው ተናግረዋል። ይሁንና ይላሉ ፕሮፌሰሩ ፣ ጭቆናና ድህነት ብቻቸውን ለህዝባዊ እንቅስቃሴ አይበቁም ፤ የግዴታ ሁኔታው በንቃተ-ህሊና መደገፍ አለበት ይላሉ።

እዚህ ላይ የተንታኞቹ አገላለጽ ከሞላ ጎደል ትክክል ብሆንም ፣ በአገራችን አፍጦ አግጦ የሚታየውን ኢኮኖሚያዊ ፣ ህብረተሰብአዊና ፣ ባህላዊ ቀውስ እንዲሁም ሙስና ከዓለም አቀፋዊ የፖለቲካና ኢኮኖሚ አወቃቀር ጋር ለማያያዝ አለመቻል ነው። እንደሚታወቀው የአቶ መለስ አገዛዝ ብቻውን የሚንቀሳቀስ ሳይሆን በፊናንስ ኦሊጋርኪው የሚደገፍና በአሜሪካን መንገስት እሹሩሩ እየተባለ ወደ ውስጥ ኢኮኖሚውንና ህብረተሰቡን በከፊተኛ ደረጃ የሚያናጋና ቀውስ ውስጥ በመክተት ፣ ወደ ውጭ ደግሞ ጦርነት ቀስቃሽ አገዛዝ ነው። አሁን ደግሞ ሌላ ትዕዛዝ በማግኘትና ህዝቡን ለማሳሳትና የስልጣኑንም ዘመን ለማራዘም ሲል የአቶ ኢሳያስን አምባገነናዊ መንግስት በጦር ማባረር አለብኝ ይላል። እጅግ አደገኛን ህዝብ አስጨራሽ አካሄድ። ከዚህም በላይ ባለፉት 20 ዐመታት የኒዎ-ሊበራሊዝምን የኢኮኖሚ ፖሊሲ ተግባራዊ በማድረግ ድህነት በከፍተኛ ደረጃ እንዲፈለፈል ያደረገ ነው። በዚህ ዐይነት የኢኮኖሚ ፖሊሲ አማካይነት የህብረተሰቡ የማሰብ ኃይል እንዲደቅ ያደረገ ብቻ ሳይሆን አዲስ ተጠቃሚ የህብረተሰብ ኃይል በመፍጠር ብሄራዊ ነጻነታችን እንዲሸረሸር ያደረገና ህልውናችንን በጥያቄ ውስጥ እንዲቀመጥ ያደረገ ነው። ይህ ሁኔታ አንድ ላይ በመጣመር ለማይቀረው ህዝባዊ እንቅስቃሴ ሁኔታውን ያመቻቸ ነው። ይሁንና ግን አገዛዙም ሆነ አቀንቃኞች በሰሜን አፍሪካና በአንዳንድ የአረብ አገሮች የታየው ዐይነት ህዝባዊ አመጽ በአገራችን ሊከሰት አይችሉም ባዮች ናቸው። በእነሱ ዕምነትም አገሪቱ በሚያስተማምን ሁኔታ ላይ የምትገኝ ነች። እስቲ የሚሉትን እንስማ።

በኢትዮጵያ ምድር እንደቱኒዚያውና የግብጹ ዐይነት ህዝባዊ እንቅስቃሴ ይከሰት አይከሰት እንደሆን ለማስታወቂያ ሚኒስተሩ ለአቶ በረከት ሰመኦን ከጋዜጠኞች ለቀረበላቸው ጥያቄ መልስ ሲሰጡ ፣ እንደዚህ ዐይነት ሁኔታ በፍጹም እንዳማይከሰት አረጋግጠዋል። የሰጡትም ምክንያት ፣ የኢትዮጵያ ህዝብ ተደስቶና ተንደላቆ የሚኖር ፣ እንዲሁም ዲሞክራሲያዊ መብቱ ሙሉ በሙሉ የተረጋገጠለት ነው በማለት ያላቸውን ዕምነት አብስረዋል። ጠቅላይ ሚኒስተር መለስ ዜናዊም ይህንን ሁኔታ በማስመር ፣ የቱኒዚያውና የግብጹ ሁኔታ በምንም ዐይነት በኢትዮጵያ ምድር እንደማይከሰትና ህዝቡም እንደማያስበው ነግረውናል። በሳቸውም ዕምነት ፣ በህዝብ የተመረጠ አገዛዝ ከስልጣኑ ሊወርድ የሚችለው ህገ-መንግስቱ በፈቀደለት በየአምስት ዐመቱ በሚካሂድ ምርጫ ብቻ ነው። ስለሆነም ይላሉ ጠቅላይ ሚኒስተሩ ፣ አገዛዛቸው ከህዝብ ለአምስት ዐመት የሚሆን የአገዛዝ ኮንትራት አግኝቷል ፤ ስልጣንም ሊለቅ የሚቻለው ከእንግዲህ ወዲያ አራት ዐመቱን ጠብቆ ነው የሚል ነው። በአስር ወራት አንድ አገዛዝ ከህዝብ የተሰጠውን አደራና ኃላፊነት ሊወጣ አይችልም ባይ ናቸው። በሳቸውም ዕምነት ፣ አንድ አገዛዝ ግዴታውን መወጣቱንና አለመወጣቱን አምስቱ ዐመቱ ሲገባደድ ብቻ ነው የሚታወቀው ይሉናል። ይሁንና ጠቅላይ ሚኒስተር መለስ ዜናዊ ለመጠየቅና እንዲነሳባቸውም የማይፈልጉት አስራዘጠኝ ዐመት ያህል በስልጣን ላይ በነበሩበት ዘመን ምን እንደሰሩ ነው። ህዝብም የሚለው ይህን ያህል ዘመን

ለውጥ ሊያመጣ ያልቻለ አገዛዝ ከእንግዲህ ወዲያ ከጥፋት በስተቀር ሌላ ሊፈጥር የሚችለው ነገር የለም ነው። ይሁንና በሳችውም አነጋገር ፣ አንድ አገዛዝ የፈለገውን በደልና ወንጀል ይፈጽም ህገ-መንግስቱን ጥሶ አገዛዙን ለመጣል የሚደረግ የማያስፈልግ ግብ ግብ ህገ-ወጥ ነው ብለው መልሰዋል። በሌላ አነጋገር ፣ ወንጀል የሚፈጽም ማንኛውም አገዛዝ ከእግዚአብሄር በታችና ከህዝብ በላይ ስለሆነ ጥያቄ ሊቀርብለትና ከስልጣን ውረድ ሊባል አይገባውም ነው የሚሉን። አንዳንድ አመጸኝነትን ከሚፈልጉ በስተቀር ከህዝቡ ዘንድ የአመጽ ሁኔታ ሊፈጠር እንደማይችል ያላቸውን ዕምነት ይገልጻሉ። ይህ ጸሀፊ የህግ አዋቂ ባይሆንም አንድ አገዛዝ እንደፈለገው ህዝብን የሚበድልና ፣ ቃል-ቂዳን በገባውም መሰረት ህዝቡን በስነስርዓት ማስተዳደር የማይችልና ለኢኮኖሚና ለማህበራዊ ቀውስ ምክንያት ከሆነ ህገ-መንግስትን ተገን በማድረግ ከህዝብ የሚመጣበትን ብሶትና እንቅስቃሴ ህገ-ወጥ ነው በማለት ህዝብን ለማታለልና ለማስፈራራት አይችልም። በአገር ውስጥ የሚደርሰው ማንኛውም የተዛባ አስተዳደርና በኢኮኖሚ ቀውስ የተነሳ የሚፈጠረው የህዝብ የኑሮ ስቃይ ከሰማይ የወረደ ሳይሆን አገዛዙ በሚከተለውና የራሱንም ህገ-መንግስት በሚቃረን መልክ በሚወስደው እግርና እጅ በሌለው የኢኮኖሚ ፖሊስ የተነሳ ብቻ ነው። ከዚህም በላይ አገዛዙ ስለህብረተሰብና ስለባህል ፖሊሲ የሚለው አንዳችም ነገር የለም። ወይም ደግሞ አንድን ህብረተሰብ በጠመንጃ ተማምኖ ከማስፈራራት በስተቀራና በከፋፍለህ ግዛው ፖሊሲ አማካይነት ከማከረባበት በስተቀር በሳይንስ በተጠና እሴት ላይ ተመስርቶ እንዴት መገንባት እንዳለበት የሚያውቀው ነገር የለም ማለት ይቻላል። ከዚህ ስንነሳ አንድ አገዛዝ እንደፈለገው ሊመጻደቀና ፣ እሱ በፈጠረው ቀውስ የህዝብ እንቅስቃሴ ቢነሳ ህገ-ወጥ ነው እያለ ሊወነጅል በፍጹም አይችልም። በታሪክ ውስጥ በአገዛዞች የተደነገገውን ህገ-መንግስት በመጣስ በህዝቦች እንቅስቃሴ አማካይነት ብዙ አገዛዞች በህዝባዊ አመጽ እንዲወድቁ ተድርገዋል። ይህም ማለት በአንድ አገር ውስጥ ፍትህ ፣ እኩልነት ፣ ዲሞክራሲና ብልጽግና እስከሌለ ድረስና ፣ አንዳንድ አገዛዞችም ሆን ብለው ዕድገት እንዳይኖርና የህዝቡ ህይወት እንዳይሻሻል እንቅፋት የሚሆኑ ከሆነ ህዝባዊ አመጽ የግዴታና የሚፈቀድም ነው። ጥያቄ ሊደረግ አይችልም ፣ ወይም ህዝቡ አያስበውም ሳይሆን መቼና እንዴት ነው የሚካሄደው የሚለው ጥያቄ ነው የፖለቲካ ተንታኞችንንም ሆነ ህዝቡን የሚያወያየው።

ይህን በማስመልከት በአገር ውስጥ የሚገኙ የበሰሉ ኢትዮጵያውያን ጋዜጠኞች ከላይ የሰፈረውን ሀቅ ነው የሚያትቱልን። በነሱም አተናተን የቱኒዚያውና የግብጹ ሁኔታ ህዝቡን በከፍተኛ ደረጃ እያነጋገረው ነው የሚል ነው። የአገሪቱ ተጨባጭ ሁኔታዎችም የሚያረጋግጡት የኢህአዴግ ኃይል ተሟጦ እንዳለቀና ህዝቡም በኑሮው እንደሚያማርር ነው። የምግብ ዋጋ በከፍተኛ ደረጃ መናር ፣ አንዳንዴም አለመገኘት ፣ የስራ ዕድል በፍጹም አለመኖር ፣ የመኖሪያ ቤት እጥረት ፣ የመመለሻ ችግርና ያሉትም በተቀላጠፈ መልክ አለመስራት ፣ በተለይም እንደ አዲስ አበባ የመሰለው ከተማ ውስጥ ህዝብ ተጨናንቆ መኖርና አሰቃቂ ወንጀሎች መፈጸም ፣ የከተማዎች መቆሸሽና መፋሰሻዎች መበላሸት ፣ የከተማዎችና መንደሮች በዕቅድ አለመሰራት ፣ የመንገዶች አሰራር የተበላሸና የተሰሩትም በአጭር ጊዜ ውስጥ ማበጥና መኪናና ሰው ተዝናንተው እንዲሄዱ አለመቻል ፣ የሚሰሩት ትላልቅ ህንፃዎች ከአገሪቱ ባህልና ታሪክ ጋር ከረዥም ጊዜ አንፃር ታስበው አለመሰራት ፣ በቂ ጠያቂና ፍላጎት ሳይኖር ሆቴል ቤቶች በብዛት መስራት ፣ በተወሰኑ የኢኮኖሚ ዘርፎች ላይ ብቻ ርብርቦሽ ማድረግና ሀብት እንዲባክን ማድረግ ፣ የእርሻ መሬትን ለውጭ „ኢንቬስተሮች" ማከራየትና ገበሬውን ከቀየው እንዲፈናቀል ማድረግ ፣ ወይም ደግሞ እጅግ በዝቀተኛ ደሞዝ እንዲሰራ በማድረግ የባርነት ሁኔታ መፍጠር ፣ ችሎታ የሌላቸው ሹመት ማግኘትና በየመስሪያ ቤቱም ሙስና መስፋፋት ፣ አንድም ነገር ካለጉቦ ማስፈጸም የማይቻልበትን ሁኔታ መፍጠርና ይህንን እንደባህል መውሰድ...ወዘተ. እነዚህ ሁሉ የአገዛዙ ባህርዮችና በየቀኑም የሚፈጠሩ ናቸው። የአገሪቱ ሁኔታ ከሞላ ጎደል ይህንን ሲመስል ፣ አገዛዙም ሆነ ካድሬዎች አገሪቱና ህዝቡ እንዳለፈላቸው ለማሳመን የማያደርጉት ጥረት ይህ ነው አይባልም። ይሁንና ግን ደግሞ በገሃድ ለመቀበልና ለማመን የማይፈልጉትን ነገር ውስጥ ለውስጥ በማውራት እንደተረበሹ ለማወቅ ተችሏል። ካድሬዎች ከህዝብ ተነጠልን እያሉ በፍርሃት እንደተዋጡ ወደ ወጭ ወጥተው የሚነገሩት ማረጋገጫዎች ናቸው። በዚህም ምክንያት የተነሳ ባለስልጣናት ልጆቻቸውንና የሚችሉትን

ሀብት ወደ ውጭ በማሸሽ ላይ እንደሆኑ ወደ ውጭ የሚወጡት ዜናዎች ያረጋግጣሉ። ይህም የሚያመለክተው አገዛዙ ወደ ውጭ ህዝቡን ለማሳመን እንደሚሞክረው ሳይሆን ሁኔታው በመብሰል ላይ ነው ማለት ነው። የሚጠበቀው ጊዜ መቼ ነው የሚገነፍለው የሚለው አነጋገር ነው።

ከዚህም ጋር በተያያዘ ረብሻ ይመጣል በሚል በየቦታው ለወላጆች ማስጠንቀቂያ እየተሰጠና ልጆም ከትላልቅ ልጆች ጋር እንዳይውሉ ወላጆች አስፈላጊውን ጥንቃቄ እንዲያደርጉ ምክርና ማስፈራሪያ እየተሰጣቸው ነው። በተጨማሪም በየቡና ቤቶችና በሆቴል ቤቶች በአንድ ጠረቤዛ ዙሪያ ከሁለት ሰዎች በላይ መቀመጥ አይፈቀድላቸውም። ይህም የሚያሳየው የአገዛዙን በጭንቀት ውስጥ መግባት ነው። ይህ በእንደዚህ እንዳለ ፣ አገዛዙ ከሁሉም የህብረተስብ ክፍል ጋር ተናክሷል። በነጋዴውና ከዚህ ቀደም አብረውት ሲበሉ ሲጠጡ የከረሙትን በሆነው ባልሆነው በማስኮረፍ የሶሻል መሰረቱን እያጠበበው ነው። ከዚህም በተረፈ በቦሌ አካባቢ ተዝናንተው የሚኖሩትን ቤታችሁን አፍርሳችሁ ፎቅ ቤት ስሩ በማለት ፍዳቸውን እንደሚያሳይ ወደ ውጭ የሚወጡት ዜናዎች ያረጋግጣሉ። ይህም የሚያሳየው አገዛዙ በደንብ የተጠና የፖለቲካ ስልት እንደሌለው ነው። ሲፈልግ ቅዱስ ፣ ሳይፈልግ ደግሞ ወደሰይጣንነት በመለወጥ ህብረተሰቡን የሚያከረባብት ነው። መላ-ቅጡ የጠፋው አገዛዝ!

እንደዚህ ባለሁኔታ ውስጥ የተቃዋሚው ኃይል ፣ በተለይም የነቃው ኃይል ሚና ርስ በርስ ከመናከስና ለስልጣን ከመስገብገብ ፣ ወይንም ውስጥ ለውስጥ ግልጽ ባልሆነ መልክ የፖለቲካና የኢኮኖሚ አጀንዳቸው ግልጽ ካልሆኑ ኃይሎች ጋር አብሮ የጋራ ግምባር ለመፍጠር መሯሯጥ ትግሉን እንደመበታተንና የህዝባችንን የስልጣኔ ጥም ለዘለዓለም ተንጠልጥሎ እንዲቀር ከማድረግ ውጭ ተነጥሎ ሊታይ አይችልም። ስለሆነም ከቡድናዊ ስሜት ባሻገር ለዚህ ፓርቲ ወይም እንቅስቃሴ ብቻ ባለማድላትና የኢትዮጵያን ህዝብ ጥቅምና የአገራችንን ህልውና በማስቀደም ወደ ውጭ ወጥቶ መታገልና መከራከር ያስፈልጋል። ለዚህ ደግሞ ፓለቲካው ከአማቱሪዝም ወደ ፕሮፌሽናልዝም የትግልና የአተናተን ስልት መቀየር አለበት። በማንኛውም የአገርና የዓለም አቀፍ ፖለቲካ ሁኔታ ላይና በኛ ላይም የሚኖረውን ተጽዕኖና የሚሸረብብንን ተንኮል እያነሱ በግልጽ መወያየት ያስፈልጋል። በዚህ መልክ ብቻ ወጣቱን ማስታማርና ህዝብን ማሰባሰብ ሲቻል ድሉም የማይቀር ብቻ ሳይሆን ፣ የአገራችንንም የወደፊት እጣ መወሰንና በቀና መስመር ላይ ማደራጀት ይቻላል። የምዕራብ አውሮፓ ታሪክ እንደሚያረጋግጥልን የብሄራዊ ነፃነት ጥያቄ ለድርድር የማይቀርብ ብቻ ሳይሆን ፣ ጠንካራ በሳይንስና በቴክኖሎጂ ላይ የተመሰረተን ኢኮኖሚ ለመገንባትና ወደ ውስጥም ህዝቡ መንፈሳዊ ሰላም እንዲቀዳጅና በራሱም እንዲተማመን ለማድረግ የግዴታ በሁሉም አቅጣጫ ፣ ማለትም በፍልስፍና ፣ በሊትሬቸር ፣ በአርክቴክቸር ፣ በቲያትር ፣ በሳይንስና በቴክኖሎጂ እንዲሁም በኢኮኖሚ ጥያቄዎች ላይ የጠለቀና ሰፋ ያለ ውይይት ማካሄድ ያስፈልጋል።

**ፈቃዱ በቀለ**

fekadubekele@gmx.de